# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**:- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

*መጋቢት 1 ቀን 2004 ዓ.ም.*

**ወያኔ የተቃዋሚ ታጣቂ ኃይሎች መሸሽጊያ ነው በሚል የአሰቦት ገዳምን በእሳት አጋየ፤**

**በጎንደር በሚገኝ የአንድ ታላቅ ገዳም ደን በኢንቨስትመንት ስም ለግለሰብ ተሸጦ ተጨፈጨፈ፤**

**በነባር የኢህዴን ካድሬዎች እና በአዲሶቹ ብአዴን ካድሬዎች መሀከል ከፍተኛ ሽኩቻ ተፈጠረ ተባለ፤**

**የወያኔ ቡድን ግራ ገብቶታል፤**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ዋና ዋና ባለስልጣናቱን አባረረ፤**

EthioLion.Com

የወያኔ ቡድን በኢንቨስትመንት ስም ለም መሬቶችን ለባዕዳን ከመስጠቱም በተጨማሪ ለብዙ ዘመናት ተከብረው የኖሩትን ደኖች እንዲጨፈጨፉ እያደረገ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ በሰደድ እሳት እንዲወድሙ እያደረገ መሆኑ ተጠቆመ::

በጋምቤላ ለዘመናት በህዝቡ ጥበቃ ሲደረግላቸው የነበሩ ደኖች በኢንቨስትመንት ስም ለባዕዳን ባለሀብቶች ተቸብችበው እንዲጨፈጨፉ ከመደረጉም በላይ ይቃወማሉ በሚል ዜጎች እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ በሰፈራ ስም እንዲፈናቀሉ ተደርጎዋል::

በምዕራብ ኢትዮጵያ በልማት ስም ደን ጭፍጨፋው ተስፋፍቶ ባለበት በዚህ ግዜ በምስራቅ ኢትዮጵያ ደግሞ የታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች መመሸጊያ ነው በሚል ለዘመናት በህዝቡ ሲጠበቅ የነበረው የአሰቦት ገዳም ደን በእሳት እንዲጋይ መደረጉ ታውቆዋል::

በምስራቅ ኢትዮጵያ በምዕራብ ሐረርጌ በሚኤሶ  የሚገኘው ደብረ ወገግ ቅድስት ስላሴ እና አቡነ ሳሙኤል የአሰቦት ገዳም ከአለማዊ ኑሮ ተለይተው ለሰማያዊው ህይወት የተዳረጉ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ መነኮሳት የሚገኙበት ሲሆን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ወያኔ የታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች መመሸጊያ ነው በሚል በእሳት እንዲጋይ መደረጉን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾል::

ከማክሰኞ የካቲት 20 ቀን ጀምሮ እስከ ሐሙስ የካቲት 22 ቀን 2004 ዓ.ም ለሶስት ተከታታይ ቀናት  የእሳት ቃጠሎው ደኑን ሲያወድም በነበረበት ወቅት ከከተማ የመጣው ህዝብ እንዳያድነው በታጣቂዎች እና በፖሊስ እንዲመለስ የተደረገ ሲሆን በገዳሙ ውስጥ ያሉ መነኮሳት አቅመ ደካማ በመሆናቸው እሳቱን በቀላሉ ሊያጠፉ ባለመቻላቸው ከፍተኛ ውድመት መድረሱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

በጥንካሬያቸው የሚታወቁት እድሜ ጠገብ እጅግ ውድ ዋጋ ያላቸው ሀገር በቀል የሆኑት ጥድ...ዝግባ... ዋንዛ... ወይራ..... ግራር.....ብሳና.....ቀረሮ.....እና ሌሎችም ዛፎች በሶስት ቀናት ውስጥ በእሳት መጋየታቸው ታውመቋ::  የወያኔ አረመኔ ቡድን የስልጣን እድሜዬን ያሳጥሩብኛል ብሎ በሚሰጋባቸው አካባቢዎች ሁሉ አላስፈላጊ እርምጃዎችን እየወሰደ በሀገር እና በህዝብ ላይ ከባድ ጉዳት እያደረሰ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ሰሞኑንም መንፈሳዊ አባቶች ብቻ በሚኖሩበት ገዳም ላይ የተቃዋሚ ታጣቂ ኃይሎች መሸሸጊያ ነው በሚል ማጋየቱ በእጅጉ የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱ ምድረ በዳ እንድትሆን አጥብቆ እየሰራ መሆኑን ያመላከተ ነው ተብሎዋል::

ቃጠሎው ማክሰኞ ዕለት ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ የተጀመረ መሆኑን የጠቆሙት በገዳሙ ውስጥ ለብዙ ዓመታት የኖሩ አባቶች እሳቱ የተነሳው ለከብት ዘረፋ ወደ ገዳሙ የገቡ የአንድ ጎሳ አባላትን ለመከላከል በተደረገ የተኩስ ልውውጥ ነው ብለው ፖሊሶች ቢናገሩም ሆን ተብሎ የተለኮሰ መሆኑን አያጠራጥርም በማለት ተናግረዋል::

ገዳሙ ሌባ  እንኩዋን ገብቶ የማያውቅበት መሆኑ እየተዋቀ የአንድ ጎሳ ሰዎች ሊሰርቁ ሲመጡ ለመከላከል በተደረገ የተኩስ ልውውጥ ተነሳ የሚባለው ለመሆኑ ለፖሊስ ማን ነግሮትስ እቦታው ሊገኝ የቻለው? እሳቱ ከተነሳ በሁዋላ ከከተማ ህዝቡ እየጎረፈ መጥቶ ሊያጠፋ ሲሞክር ለምን ተከለከለ? በማለት የገዳሙ አባቶች ጥያቄዎቸ ያቀርባሉ:: ከዚህ ቀደም የወረዳው አስተዳዳሪን ጨምሮ በተከታታይ እየመጡ የታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች መሸሸጊያ ናችሁ በማለት አውጫጪኝ ሲያስቀምጡን የነበረ በመሆኑ አሁንም ከዚሁ ጋር በተያያዘ እሳቱን  ያስነሱት እነሱ መሆናቸው ጥርጥር የለንም ሲሉ በአንድ ቃል አባቶቹ ተናግረዋል::

ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ በ2001 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ ቲታጣቂዎች ወደ ገዳሙ ገብተዋል ተብሎ 13 ሺህ ሔክታር የሚሸፍነውን ደን በእሳት እንዲጋይ አድርገው ከግማሽ በላይ እንዲወድም የተደረገ ሲሆን አሁንም ለዘረፋ የመጡትን ለመከላከል በተደረገ የተኩስ ልውውጥ የተነሳ ቃጠሎ ነው መባሉ ከጉንጭ ማልፋት ባሻገር የሚታመን አይደለም ሲሉ የገዳሙ አባቶች እንባ እየተናነቃቸው ይገልጻሉ::

EthioLion.Com

በጎንደር የሚገኘው አንድ ታላቅ ገዳም ለኢንቨስትመንት ነው በሚል ይዞታው ተቀምቶ ለዘመናት ተጠብቆ የነበረውን የገዳሙ ደን በግሬደር እንዲገረሰስ የተደረገ ሲሆን ወድመቱን የተቃወሙ የገዳሙ አባቶችም በፌዴራል ፖሊስ ታፍሰው ወዳልታወቀ ስፍራ እንዲወሰዱ መደረጋቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

በየገዳማቱ ላይ የሚደርሰውን ውድመት እና ዝረፊያ ለመከላከል ያልቻሉት ..... ሰምተው እንዳልሰሙ .....አይተው እንዳላዩ ሆነው የካድሬነት ስራቸውን እየሰሩ ብቻ እድሜያቸውን እያራዘሙ የሚገኙት አባ ጳውሎስ በአሰቦትም ሆነ በጎንደር ገዳማት ላይ የደረሰውን አደጋ ተከትሎ አንዳችም ሀሳብ አለመሰንዘራቸው በእጅጉ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያሳፍር መሆኑን በየገዳማቱ ያሉ አባቶች በቁጭት እና በሀዘን እየተናገሩ ይገኛሉ::

በጋምቤላ ባለፈው ዓመት ብቻ ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች ከ100 ሺህ ሄክታር በላይ ሸጠውላቸው ከግማሽ በላይ ደኑ እንዲጠረግ ተደርጎ የወደመ መሆኑን ተከትሎ ዜጎች ከመኖሪያ ቀዬአቸው ተፈናቅለው ባለበት በዚህ ግዜም እስከ ዛሬ ድረስ ባለሀብቶቹ ወደ ስራም እንዳልገቡ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማም አብራርቶዋል::

በወለጋ ውስጥ ዴዴሳ በረሀ ላይ ከትሞ የነበረውን ደን ለወያኔ በረሀ አመጣሽ ጄኔራል መኮንኖች የእርሻ ልማት ማስፋፊያ በሚል ደኑ ተመንጥሮ እንዲሰጣቸው በመደረጉ አካባቢው ከለምነት ወደ ምድረ በዳነት ተቀይሮ ያለበት ወቅት ላይ እንደተደረሰና የአካባቢው ህዝብም በአሁኑ ሰዓት እየተሰደደ ወደ መሀል ከተማ ለልመና እየተዳረገ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሎዋል::

ይህንንና መሰል ግፎች በህዝብ እና በሀገር ሀብት ላይ እየፈጸመ ያለው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የአየር ብክለትን ለመቀነስ በሚል ከአፍሪካ ተወክሎዋል ተብሎ በየስብሰባው ላይ የሚገኝ ቢሆንም ለዘመናት በአባቶቻችን ተጠብቆ የኖረውን ደን እያወደመ ከማጋየቱም ባሻገር ለባለሀብቶች እየቸበቸበ ሀገሪቱን ምድረ በዳ እያደረገ ይገኛል::

በሌላ ዜና ብአዴንም እንደ ኦህዴድ እና ደኢህዴን ተለጣፊ ካድሬዎች ሁሉ ምንጠራ ለማድረግ በክልሉ ውስጥ የምክር ቤቱ ስብሰባ መጀመሩ ከባህር ዳር የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ሰኞ የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም በተጀመረው የአማራ ክልል ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ሹም ሽረት እንደሚደረግና በተለይ የወቅቱ የመለስ ዋነኛ አቀንቃኝ እና ቀኝ እጅ ለሆነው በረከት ስመኦን ደጋፊዎች ናቸው የተባሉትን ወጣት ካድሬዎች በተለያዩ መልኩ ወደ ስልጣን የማምጣት ስራ ይሰራል ተብሎም በምስጢር እንደተያዘ ይሄው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ለአምስት ቀናት እንደሚቆይ የተነገረለት ይሄው የአማራ ክልል ምክር ቤት በነባር የኢህዴን ካድሬዎች እና በአዲሶቹ ብአዴን ካድሬዎች መሀከል ከፍተኛ ሽኩቻ ይደረጋል ተብሎ ቢጠበቅም በአሁኑ ሰዓት የቀድሞ የኢህዴን ታጋዮች የነበሩ ባለስልጣናት ተመናምነው በአዲሶቹ ብአዴኖች የተተኩ በመሆኑ በሚተላለፈው ውሳኔ ላይ ጫና ቢፈጥሩም በድምጽ ብልጫ ሊበለጡ እንደሚችሉ አስቀድሞ የተሰራ በመሆኑ ብዙ ተፅዕኖ እንደማይፈጥሩ ከወዲሁ እየተነገረ ይገኛል::



EthioLion.Com

በተለይ ከስድስት ወር በፊት በክልሉ የሚሰሩ አፍራሽ ተግባራት ላይ መወያየት አለብን.....መሬት ለባለ ሀብቶች እየተባለ ተገምሶ የሚሰጥበት መንገድ መቆም አለበት...የጎረቤት ሀገራት ዜጎች ሲወጡና ሲገቡ እንዳሻቸው መፈንጫ መሆኑ ቀርቶ ገደብ ሊበጅለት ይገባል.....የባለስልጣናት ስልጣን ገደብም ሊወሰን ግድ ይላል .....ለክልሉ የሚመደበው በጀት እና አፈጻፀሙም ግልጽ መሆን አለበት .....በሚሉና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የኢህዴን ነባር ታጋዮች አቅርበው የነበረው ጥያቄ በምክር ቤቱ ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ውይይት ሊገባ በነበረበት ወቅት መለስ ዜናዊና በረከት ስምኦን ድንገት ባስተላለፉት ተዕዛዝ ለአሁኑ ስብሰባ ተላልፎ ሊቁዋረጥ እንደቻለ የደረሰን ዘገባ ገልፆ ይሄው አጨቃጫቂና አነታራኪ ነው የተባለለት አጀንዳ ሰሞኑን ለውይይት እንደሚቀርብ ዘገባው አስታውቆዋል::

የዳኝነት ሹመቱን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በችሎታ ሳይሆን በሚፈጽመው የፖለቲካ ቁርጠኝነት ነበር ያሉት ተሰብሳቢዎቹ በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ ግፍ እና በደል እየፈጸሙ ያሉት ካድሬ ዳኞች በመሆኑ ይሄም አንድ መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል በሚል በነባር የኢህዴን ታጋዮች ቀርቦ የነበረ ሲሆን ይሄም በአሁኑ ስብሰባ ላይ ይነሳል ተብሎ ከሚጠበቁት ጥያቄዎች መሀከል አንዱ እንደሆነ ዘገባው ዘርዝሮዋል::

በተለይ በብአዴን ውስጥ ትልቁን ሚና እየተጫወተ የሚገኘው በረከት ስምኦን ወጣት ካድሬዎቹን በጥቅማ ጥቅም እየደለለ በመያዝ የራሱ ደጋፊ እያደረጋቸው መሆኑን በቁጭት እየተናገሩ የሚገኙት ነባር ታጋዮቹ በአሁኑ ሰዓት አድራጊ ፈጣሪ የሆነው እሱና እሱ ብቻ በመሆኑ አሁንም የስብሰባውን አጀንዳ አዲስ አበባ ላይ ተቀምጦ ሊቀይረው ይችላል ሲሉ አስቀድመው ያላቸውን ግምት እየተናገሩ ይገኛሉ::

ነባር የኢህዴን ባለስልጣናት በክልሉ የተፈጸሙትን ምዝበራና የተለያዩ ስህተቶች አንድ በአንድ ዘርዝረው ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው የክልሉ ፕሬዝዳንት የሆነው አያሌው ጎበዜ በመሆኑ ከስልጣኑ እንዲነሳ በምክር ቤት ደረጃ ተወስኖ ያለቀለት የነበረ ቢሆንም በረከት ስምኦን ድንገት በስብሰባው ላይ በመገኘት ውሳኔው እንዲጉዋተት እና በይደር እንዲሆን አድርጎ በማሳለፉ በወቅቱ ውሳኔው ተግባራዊ ካለመደረጉም በተጨማሪ ምርጫ 2002ን ተከትሎ እንደገና የክልሉ ፕሬዝዳንት ሆኖ እንዲቀጥል በመለስ ሹመቱ እንዲጸድቅለት መደረጉንም ዘገባው ጨምሮ አስታውሶዋል::

ዛሬም ምንም ሆነ ምንም ካድሬዎቹ ቢንጫጩም መለስና በረከት በፈለጉት መንገድ እስካልሄደ ድረስ ነባር ታጋዮቹ ያቀረቡት አንዱም ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ውሳኔ ይሰጥበታል ማለት ዘበት ነው የሚል አስተያየት ይሰጣል::

በአሁኑ ሰዓት የሀገሪቱን ስልጣን ሙሉ ለሙሉ መለስ ዜናዊና ሚስቱ እንዲሁም በረከት ስምኦን ብቻ ጠቅልለው እንዳሻቸው እያደረጉ ያለበት ደረጃ ላይ በመድረሳቸው ብዙዎቹ ነባር የህወሀት እና የኢህዴን ታጋይ ባለስልጣናት ያኮረፉበት ወቅት መሆኑ ይታያል ሲሉ ታዛቢዎች አስተያየታቸውን ይሰጣሉ::

መለስ ዜናዊ ይሄንኑ ችግር ለማርገብ በሚል ከቅርብ ቀን ወዲህ በሲቪልና በወታደራዊ ከፍተኛ መኮንኖች ላይ ውስጣዊ ሹም ሽር እያደረገ ሲሆን በተለይ የአንድ መንደር ሰዎችን ብቻ በምስጢር

እያሰባሰበ በዙሪያው እየኮለኮላቸው የሚገኝ ሲሆን በረከት አፍለኛ ካድሬዎችን ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን እያስያዘ የራሱን ደጋፊዎች እያሰባሰበ ነው ይባላል።

መለስ ያለ አንዳች ሀፍረት የራሴ ናቸው የሚላቸውን የኮሎኔል ማዕረግ ያላቸውን መኮንኖች ጄኔራል እያደረገ እየሾማቸው በምስጢር ወደ ስልጣን እያመጣቸው መሆኑ በህወሀት ነባር መኮንኖች እና ባለስልጣናት ዘንድ ኩርፊያ ማስከተሉም እየተነገረ ይገኛል።

በስራ ላይ የነበሩት ጥቂት የኢህዴን ነባር መኮንኖች በጡረታ ስም ከመከላከያ ውስጥ እራሳቸውን እንዳገለሉ አድርገው እያስገደዱ በማስፈረም የተወሰነ ደራጎት ክፍያ እየተሰጣቸው እየተሰናበቱ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአዲሱ ምስጢራዊ ሹመት ውስጥ የተካተቱ ጥቂት የበረከት አድናቂና ተከታይ የሆኑ መኮንኖችም የጄኔራልነት ማዕረግ እንደተሰጣቸው ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

የወያኔ ቡድን በመላ ሀገሪቱ ባለስልጣናቱን እያመሰ ባለበት በዚህ ግዜ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ በበኩሉ ሰሞኑን አዲስ ሹም ሽረት ማድረጉን ከከንቲባው ጽህፈት ቤት ሾልኮ የወጣው ዘገባ ገለፀ።

ከተሾሙ ሶስት ወራትን ያላስቆጠሩና ገና ስራውን በአግባቡ መስራት ያልጀመሩትን ጨምሮ ከአስር በላይ ከፍተኛ የከተማዋ አመራሮች ከስልጣናቸው መባረራቸውን ይሄው የደረሰን ጥቆማ ገለፀ።

ስር የሰደደው የወያኔ የዘረኝነት እና አምባገነን ስርዓት በፈጠረው ዝርክርክ አሰራር እና በሚፈጽመው ሙስና ህዝቦችዋን ለድህነት የዳረገ ከመሆኑም በተጨማሪ አይን ያወጣ አድልኦ እየተፈጸመ በለበት በዚህ ግዜ ስርዓቱ እራሱን ችሎ መንቀሳቀስ አቅቶት ጠዋት የሾማቸውን ከሰዓት እያባረራቸው መያዣ መጨበጫ ማጣቱን የሰሞኑ ድርጊቱ እየመሰከረ መሆኑ ታውቆዋል።

ሰሞኑን በደቡብ፤ በኦሮሚያ እና በአፋር የተደረገው የሹም ሽረት ተቀጣጥሎ አሁን ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ላይ ተቀምጠው የነበሩትን እያንሳፈፈ በነበረከት ስምኦን ተመልምለው ኮርስ የተሰጣቸው ወጣት ካድሬዎች ቦታ ቦታውን እንዲይዙ መደረጉ ታውቆዋል።

ግራ የገባው ኩማ ደመቅሳ አሁን የተባረሩትን ሹማምንት ከሶስት ወር በፊት እውቅና ሰጥቶ ሾሙዋቸው የነበረ ቢሆንም እራሱ የሰጣቸውን ሹመት ቀምቶ በሶስት ወር ግዜ ውስጥ መልሶ ያባረራቸው ሲሆን የተራበውን ካድሬ እያመጣ ጠግቦ እንዲመለስ እያደረገ በህዝብ እና በሀገር ሀብት ላይ እያላገጠ መሆኑን ህዝቡ በምሬት እየተናገረ ይገኛል።

ሰሞኑን በተደረገው ሹም ሽረት የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ስራ አስኪያጁ ኃይሌ ፍስሀ፤ምክትል ስራ አስኪያጁ አበበ ዘልዑል፤የመሬት አስተዳደር ግንባታና ፍቃድ ባለስልጣን ኃላፊ ቃሲም ፊጤ፤ምክትል ኃላፊው ይርጋለም ብርሀኑ፤የመሬት ልማት ባንክ እና ከተማ ማደስ ምክትል ስራ አስኪያጅ አለማየሁ አለሙ፤የከተማ ፕላንና መረጃ ተቋዋም ምክትል ስራ አስኪያጅ ሳህሌ ሰርሻ

EthioLion.Com

፧ዲዛይንና ግንባታ ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አበበ ከበደ ፧የአቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ አባተ ስጦታው ፧የትራንስፖርት አደረጃጀት ስምሪት ኃላፊ ሽብሩ ቀልቤሳ ከስልጣናቸው ሙሉ ለሙሉ የተባረሩ ሲሆን በምትካቸው ሌሎች ወጣት የበረከት ምልምሎች ቦታውን እንደያዙ ከከንቲባው ጽህፈት ቤት ሾልኮ የወጣው ጥቆማ አጋልጦዋል::

ከሶስት ወር በፊት በግምገማ ተነሳ ተብሎ ከስልጣኑ የተባረረውን ምክትል ከንቲባ ከፍያለው አዘዘን ተክቶ የተሾመው አባተ ስጦታው የተባለው የብአዴን ሰው ሰሞኑን ደርቦ ይዞት ከነበረው የአቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊነት ተወግዶ በመጨረሻ ማስጠንቀቂያ በምክትል ከንቲባነት እንዲቆይ መደረጉ ታውቆዋል::ይህን ግለሰብ በረከት ስምኦን ያመጣው በመሆኑ ከስልጣኑ እንደ ሌሎቹ ሙሉ ለሙሉ ሳይወገድ ቀርቶዋል::

ከነዚህ ከፍተኛ የከተማዋ ባለስልጣናት በተጨማሪ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ውስጥ የሚሰሩ አመራሮችም ከስልጣናቸው የተነሱ ሲሆን በቅርቡም በምትካቸው ሌሎች አፍለኛ ካድሬዎች እንደሚመደብ ታውቆዋል::በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ ወያኔ ውስጥ ውስጡን እየተሰመሰ በመሆኑ አስተዳደራዊ ስራዎች ቆሞ ህዝቡም ለእንግልት ተዳርጎ ይገኛል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ስርዓቱ በሙስና መጨማለቁን አምኖ...... ባለስልጣናቱ በገንዘብ ማበጣቸውን ገልጾ...... ለህዝብ ይፋ ቢያደርግም አንዳችም እርምጃ ለመውሰድ ካለመቻሉም በተጨማሪ ያልጠገበው ባለ ተረኛ እየወጣ የራሱን ድርሻ እያፈሰ እንዲወስድ ከማድረግ ባሻገር አንዳችም ውሳኔ ያልሰጠ ሲሆን ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት እራሱ በሚስቱና በልጆቹ ስም በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር አፍሶ ውጭ ሀገር እያከማቸ በመሆኑ ጣቱን ወደ ሌላ ሊቀስር ከቶ አይቻለውም በማለት ታዛቢዎቸ እየተናገሩ ይገኛሉ:: ከዚህ በፊት የወያኔ ቀንደኛ ሹሞች አበተ ኪሾ 71 ሚሊዮን ብር ያረጋል አይሸሹም 86 ሚሊዮን ብር በመስረቅ መከሳሰቸው ቢነገርም የሰረቁትን ገንዘብ ለማስመለስ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ወያኔ የሌቦች ጥርቅም መሆኑን በግልጽ እንደሚያሳይ ይናገራሉ::

በመጨረሻም በእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ ሲፎክር እና ሲያቅራራ የነበረውና ንቅናቄው ያስፈራው የወያኔ እብሪተኛ ቡድን ሰሞኑን በይፋ ይቅርታ ጠይቆ ያቀረቡትንም ጥያቄ በአጭር ግዜ መልስ እንደሚሰጥ መግለፁ ታወቀ::

በአወሊያ ኮሌጅ ውስጥ የተጀመረው የተቃውሞ ንቅናቄ ቀስ በቀስ ወደ ሌሎች ክልሎች በመዛመቱና በመዳረሱ ስጋት የገባው የወያኔ እብሪተኛ ቡድን የእስልምና እምነት ተከታዮች ያቀረቡትን ጥያቄ በአጭር ግዜ እንደሚመልስ በይፋ መግለፁ ታውቆዋል::

የወያኔ አባል የሆኑ የእስልምና ምክር ቤት ፕሬዝዳንት እና አመራሩ እንዲነሱ...... የአወሊያ ኮሌጅ ከዚህ ቀደም በነበረበት ሁኔታ እራሱን ችሎ ከየትኛውም አካል ጥገኛ ሳይሆን በነጻነት እንዲቀጥል......አህባሽ የተባለው መጤ ሀይማኖት ወያኔ እያስፋፋ ያለውን እንዲያቆምና በአስቸኳዋይ እንዲሰረዝ የሚሉና ሌሎች አንገብጋቢ ጥያቄዎች ማንሳታቸውን ተከትሎ ወያኔ ከፋፍሎ ለመምታት ብርቱ ጥረት ቢያደርግም በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ህብረት እና አንድነት በመፈጠሩ የተነሳ ስጋት ስለገባው ሳይወድ በግዱ አምኖ ይቅርታ ሊጠይቅ ቸሎዋል::

EthioLion.Com

ከውስጥ እና ከውጭ የስንግ ተወጥሮ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በቅርቡ ያወጣው የሊዝ አዋጅን ተከትሎ ህዝቡ የሚያነሳው ጥያቄ የውስጥ እግር እሳት ሆኖ እያንገበገበው ባለበት ወቅት የአወሊያ ኮሌጅ እና ትምህርት ቤቶችን በካድሬዎች ቁጥጥር ስር ለማድረግ ዘመቻ የጀመረ ቢሆንም መላው የእስልምና እምነት ተከታዮች በሙሉ አንድ በመሆን ወያኔን በመቃወማቸው እና አቋዋም በመወሰዳቸው ስጋት ስለገባው ይቅርታ ጠይቆ ለጠየቁት ጥያቄም አስቸኩዋይ መልስ ለመስጠት ቃል መግባቱ ወያኔ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳለ የሚያመላክት ነው ሲሉ የሙስሊም እምነት አማኞች ገለፁ::

በህዝብ ላይ ሲቀልድ እና ሲፈነጭ የነበረው አምባገነኑ የወያኔ ቡድን በለመደው መንገድ የሙስሊሙን  ማህበረሰብ ከፋፍሎ ሊመታና ሊያንቀጠቅጥ አስቦት የነበረው እቅድ በመክሸፉ በመበሳጨት ሳይወድ በግዱ ይቅርታ ከመጠየቁም በላይ በአጭር ግዜ የምክር ቤቱ ምርጫ እንደሚያደርግ በይፋ በሚቆጣጠራቸው ቲሌቪዥን እና ራዲዮ መግለፁ በህዝቡ ዘንድ እያነጋገረ ይገኛል::

ከሀገሪቱ ካዝና ወጪ በማድረግ ከውጭ ሀገር ድረስ በዶላር እየከፈለ ባስመጣቸው መምህራኖች በመላ ሀገሪቱ በግዴታ አህባሽ የተባለ አዲስ መጤ ሀይማኖት እንዲማሩ ያደረገ ቢሆንም ሙስሊሙ ቀድሞ በመንቃቱ ድርጊቱን ከማውገዝ አልፎ እንፋለማለን በማለቱ የደነገጠው ወያኔ ድንገት ከያዘው አቋዋም ሊቀለብስ እንደቻለም ሙስሊሙ ማህበረሰብ  እየገለፀ ይገኛል::

ጥቂት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ለሆዳቸው ያደሩ ግለሰቦችን _በመያዝ አዲሱን ከሊባኖስ እንደመጣ የሚነገርለትን አህባሽ የተባለ እምነትን ሊያስፋፋና ሙስሊሙን ሊከፋፍል የነበረው ወያኔ  በሙስሊሙ አንድነት የከሸፈበት ሲሆን የአወሊያ ኮሌጅ ተማሪዎች ያነሱት የመብት ጥያቄንም ሳይወድ በግዱ ተቀብሎ ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ ጥሪ ማቅረቡ የወያኔ አከርካሪ በሙስሊሙ አንድነት እንደተመታ ገልፀው ሌላውም የሀገሪቱ ዜጋ ከሙስሊሙ ተምሮ በአንድነት እና በህብረት ወያኔን ዞር በል ሊለው ይገባል ሲሉ የሙስሊም ማህበረሰብ በአደባባይ እየገለፀ ይገኛል::

EthioLion.Com